ይዘጋጁ

KING አውራጃ

King County
Emergency Management

ዕውቅናዎች

በሚከተሉት የተሠራ

Susanna Trimarco፣ የKing አውራጃ የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር፤ Kayla Sainati፣ ከTukwila ከተማ፤ Shannon Kirchberg፣ ከDes Moines ከተማ፤ Will Lugo፣ ከSeaTac ከተማ፤ እና Sophia Lopez፣ ከSeattle ከተማ

ከሚከተሉት እገዛን በመቀበል

Ellen Montanana፣ ከBellevue ከተማ፤ Albi Pacewiczh፣ ከIssaquah ከተማ፤ Shaunise Sowders፣ የKing አውራጃ የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር፤ እና Jim Schunke፣ ከPacific ከተማ።

የፋይናንስ ድጋፍ

የKing አውራጃ Office of Emergency Management (የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ቢሮ) ለዚህ ሕተመት የFEMA የገንዘብ ድጋፍ በAssistance Listing Number (እርዳታ ዝርዝር ቁጥር, ALN) 97.067 በኩል እውቅና ሰጥቷል። ነገር ግን፣ ይህ ሕትመት FEMAን የሚያስተዋውቅ ወይም የFEMAን እይታዎች የሚያንፀባርቅ አይደለም።

ልዩ ምስጋና

Listos California እጅግ በጣም ጥሩ የሆነውን የሥራ ደብተራቸውን እንደ ይዘት ልማት መሠረት ስለተጠቀሙ ልዩ ምስጋና ይገባቸዋል።

በKing አውራጃ ውስጥ ላሉ ለማህበረሰብ ተደራሽነት የሥራ ቡድን እና የሕዝብ ትምህርትን ለሚደግፉ ሁሉ ልዩ ምስጋና።

ለማንኛውም ዓይነት አደጋ ይዘጋጁ

1. ማንቂያዎችን ያግኙ እና ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይወቁ።

2. የእርስዎን ሰዎች ደኅንነት ለመጠበቅ ዕቅድ ያውጡ።



3. የሚፈልጉትን ነገሮች ይዘው መሄድ ወደሚችሉበት ቦርሳ ላይ ያዘጋጁ።

4. የአደጋ ጊዜ የአቅርቦት ኪት ያዘጋጁ።

5. ጓደኞች እና ጎረቤቶች እንዲዘጋጁ ይርዷቸው።

6. በተጨማሪ ግብዓቶች የበለጠ ይማሩ።

7. አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ።

1. ማንቂያዎችን ያግኙ እና ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይወቁ

የአደጋ ጊዜ ማንቂያዎችን ለማግኘት ይመዝገቡ። ወደ **kingcounty.gov/alert** ወይም ወደ አካባቢዎ የአደጋ ጊዜ ማሳወቂያ ሥርዓት ይሂዱ። በ **kingcounty.gov/localEM** ላይ ስለአካባቢዎ ስልጣን ማንቂያ ሥርዓት መረጃ ያግኙ።

የእኔ የአካባቢ ማንቂያ ሥርዓት የሚከተለው ነው፦

የአካባቢ ማንቂያ ሥርዓት

....

ሌሎች የማንቂያ ሥርዓቶች (በምሥራበት፣ በምዲዝበት፣ በምጫወትበት ቦታ ላይ፣ ወዘተ)

....

ሊያምኑት የሚችሉት የዜና ምንጭ ያግኙ

አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ምን እየተከሰተ እንዳለ ማወቅ እና ምን ማድረግ እንዳለብዎት እና የት መሄድ እንዳለቦት ወቅታዊ መረጃ ማግኘት አለብዎት። ይህንን መረጃ ለማግኘት ብዙ መንገዶች አሉ።

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ መረጃን የሚጋሩ የአካባቢ ሬዲዮ ጣቢያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

KIRO 710 AM	**KOMO 1000 AM**
KPLU 88.5 FM	**AM 1610**

የአደጋ ጊዜ ግብዓቶች ድር ጣቢያዎች

WA211.org | **KCEmergency.com**

የአካባቢ/የካውንቲ የድንገተኛ አደጋ መረጃ ለማግኘት እዚህ ይመልከቱ

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ መረጃን ለማግኘት ተጨማሪ መንገዶችን ለማግኘት የአካባቢዎን ስልጣን ድረ-ገጽ ይመልከቱ።

2. የእርስዎን ሰዎች ደኅንነት ለመጠበቅ ዕቅድ ያውጡ፦ ይገናኙ እና ጥበቃ ያድርጉ

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ከማን ጋር መገናኘት እንደሚፈልጉ ያስቡ። የቅርብ ቤተሰብን፣ ጓደኞችን፣ ጎረቤቶችን ወይም ተንከባካቢዎችን ዝርዝር ያዘጋጁ። በዝርዝሮችዎ ውስጥ ላሉ ሁሉ ቅጂዎችን ያጋሩ።

በዕውቂያ ዝርዝርዎ ውስጥ፣ እርስዎ ከሚኖሩበት አካባቢ ውጭ የሆነ በአካባቢዎ አደጋ የማይጎዳ አንድ ሰው ያካትቱ። በአደጋ ጊዜ፣ የአካባቢው የአውታረ መረብ ማማዎች ሲጨናነቁ እና አካባቢያዊ ጥሪዎች ላይገናኙ ይችላሉ። እርስዎ እና የሚወዷቸው ሰዎች ደኅንነታችሁን፣ የት እንዳላቹ እና ሌሎች አስቸኳይ መረጃዎችን ለማሳወቅ ከአካባቢው ውጪ ካለ ዘመድ ወይም ጓደኛ ጋር መገናኘት ይችላሉ።

የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዕውቂያዎች

የዕውቂያ ስም	
የሞባይል ስልክ	የቤት ስልክ
የሥራ/የትምህርት	ኢሜይል
አድራሻ	
የዕውቂያ ስም	
የሞባይል ስልክ	የቤት ስልክ
የሥራ/የትምህርት	ኢሜይል
አድራሻ	
የዕውቂያ ስም	
የሞባይል ስልክ	የቤት ስልክ
የሥራ/የትምህርት	ኢሜይል
አድራሻ	

ከአካባቢው ውጪ ያሉ ዕውቂያዎች

ከአካባቢው ውጪ ያለ ዕውቂያ ስም
የሞባይል ስልክ
የቤት ስልክ
ኢሜይል
የሥራ/የትምህርት
አድራሻ

በአደጋ ጊዜ የአካባቢያዊ ስልክ ጥሪዎች እየሠሩ ካልሆነ **የጽሑፍ መልዕክት** ለመላክ ይሞክሩ።

የሞባይልዎን **የስልክዎ ቻርጅ መሙያ እና የመጠባበቂያ የባትሪ ምንጭ** ያስቀምጡ።

2. የእርስዎን ሰዎች ለመጠበቅ ዕቅድ ያውጡ፦ የመልቀቂያ ዕቅድ

በአደጋ ጊዜው ወቅት ቤትዎ፣ ትምህርት ቤትዎ ወይም የሥራ ቦታዎ ደኅንነቱ ካልተጠበቀ፣ ከሚያስቡላቸው ሰዎች ጋር ለመገናኘት ወደ ደኅና ቦታ መሄድ ያስፈልግዎታል። ከአደጋው በፊት፣ ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ደኅንነቱ የተጠበቀ የመሰብሰቢያ ቦታ ይምረጡ። ቦታውን በታተመ ወይም በወረቀት ካርታ ላይ ምልክት ያድርጉበት። የወረቀት ካርታው የአውታረ መረብ አገልግሎት በማይኖርበት ጊዜ ደኅንነትዎ ወደሚጠበቅበት ቦታ እንዲደርሱ ሊረዳዎት ይችላል።

ቀድመው ያቅዱ። ወደ ቤተሰብ መሰብሰቢያ ቦታዎ በጣም አስተማማኝ የሆኑትን መንገዶች ይወቁ።

1. የአካባቢ ባለስልጣናትን መመሪያ ይከተሉ።

መመሪያዎች ከእርስዎ የእሳት አደጋ ክፍል፣ ከሕግ አስከባሪዎች፣ ከከተማ ወይም ከካውንቲ ባለስልጣናት በአደጋ ጊዜ ማንቂያዎች፣ በማህበራዊ ሚዲያ እና በዜና ስርጭቶች ሊመጡ ይችላሉ።

በአደጋ እና በድንገተኛ ጊዜያት ወቅት መረጃን ለማግኘት ለአካባቢያዊ ማንቂያዎች **kingcounty.gov/alert** ላይ ይመዝገቡ። ስለ አካባቢያዊ ማንቂያ ሥርዓቶች ለማወቅ ወደ **kingcounty.gov/localEM** ይሂዱ።

2. ከቤትዎ ወይም ከማህበረሰብዎ በፍጥነት ለመውጣት የተለያዩ መንገዶችን ይማሩ።

በአደጋ ጊዜ፣ ደኅንነትዎ ወደሚጠበቅበት ቦታ የሚወስደው መንገዱ እርስዎ የለመዱት መንገድ ላይሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ የሚሄዱባቸውን መንገዶች እና የአውቶቡስ መንገዶች በአደጋዎች ምክንያት ሊዘጉ ይችላሉ። በአደጋ ጊዜ ሊሄዱባቸው የሚችሏቸውን ተጨማሪ መንገዶችን ይወቁ።

3. ወደ ቤተሰብ መሰብሰቢያ ቦታዎ ለመሄድ ዝግጁ ይሁኑ።

የአደጋ ጊዜ ቦርሳ ውስጥ የሚኖሩ ዕቃዎቸን እንደተዘጋጁ ያቆዩ (ገጽ 8-9)። የሚያስቡላቸው እና ስለእርስዎ የሚያስቡልዎትን ሰዎች ያግኙ። ወደ ቤተሰብ ወይም ጓደኞች ቤት መድረስ የሚቻል እና ደኅንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ይወስኑ። ካልሆነ ደኅንነቱ የተጠበቀ ቦታ ይፈልጉ።

ከእርስዎ ጋር አብረው ከሚሄዱ ሰዎች ጋር መሄድን ይለማመዱ። በዚህ መንገድ፣ በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እንዴት አንድ ላይ እንደሚመሆኑ ያውቃሉ።

ከአካባቢው ውጭ ከሚኖረው ዕውቂያዎን መገናኘትን ይለማመዱ።

2. የእርስዎን ሰዎች ደኅንነት ለመጠበቅ ዕቅድ ያውጡ፦ የአካባቢ አደጋ ግብዓት መመሪያ

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ሊረዱዎት የሚችሉ አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮችን እና የድርጅቶችን ድረ-ገጾች ይጻፉ።

ለድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚጠቅሙ ጥሩ ዕውቂያዎች

የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**
የሼሪፍ(አካባቢያዊ ሕግ አስከባሪ)/ፖሊስ ክፍል	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**
የአካባቢያዊ ድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ኤጀንሲ	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**
የሕዝብ ትራንስፖርት ኤጀንሲ	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**
የመድን ኩባንያ	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**
የፍጆታ ኩባንያ	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**
ሌላ	
ስልክ	**ድር ጣቢያ**

የእርስዎ አስፈላጊ ቦታዎች

የድጋፍ ድርጅቶች

ስልክ

ድር ጣቢያ

የድጋፍ ድርጅቶች

ስልክ

ድር ጣቢያ

የድጋፍ ድርጅቶች

ስልክ

ድር ጣቢያ

911 የመረጃ ምንጭ **አይደለም**። ለድንገተኛ አደጋ ጊዜ መረጃ ለማግኘት ወደ **211 ይደውሉ**።

3. የሚፈልጉትን ነገሮች ይዘው መሄድ ወደሚችሉበት ቦርሳ ላይ ያዘጋጁ፦ ቀድመው እቃዎችዎን ያዘጋጁ

አብዛኛዎቹ አደጋዎች ያለማስጠንቀቂያ ይከሰታሉ። ለመግዛት ወይም ለማዘጋጀት ጊዜ ላይኖርዎት ይችላል። እርስዎ እና የሚወዷቸው ሰዎች ድንገተኛ አደጋ ቢከሰት የሚፈልጉትን እንዲያገኙ ለእያንዳንዱ የቤተሰብዎ አባል አስፈላጊ ነገሮችን ለማሸግ አሁን የተወሰነ ጊዜ ይውሰዱ።

አሁን ያዝጋጁ

ሰነዶች

- የመታወቂያ እና የመድን ቅጂዎች።
- ለእርስዎ አስፈላጊ የሆኑ ካርታዎች፣ ሕጋዊ ሰነዶች እና ሌሎች ወረቀቶች።
- የቤተሰብ እና የቤት እንስሳት ፎቶዎች።
- የዚህን የተጠናቀቀ መመሪያ ቅጂ ያካትቱ።
- ዲጂታል ቅጂዎችን እና ወረቀትን ግምት ውስጥ ያስገቡ። ዲጂታል ቅጂዎች ደኅንነታቸው የተጠበቀ እና በይለፍ ቃል የተጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ጥሬ ገንዘብ

- ዝርዝሮች ቢሆኑ የተሻሉ ናቸው፣ በተለይም የ$1 እና $5 ገንዘቦች
- በበጀትዎ ውስጥ ይቆዩ፣ በየጊዜው ጥቂት ዶላሮችን ይቆጥቡ።

ካርታ

- የሰፈርዎ የወረቀት ካርታ ላይ የተለያዩ መንገዶች ላይ ምልክት ያድርጉ።

የመድሐኒት ዝርዝር



- ሁሉንም የመድሐኒት ማዘዣዎች ይዘርዝሩ።
- እንደ አለርጂ፣ የሕክምና ሁኔታዎች፣ አስፈላጊ አቅርቦቶች እና መሣሪያዎች እና የዶክተርዎ ቢሮ መረጃ ያሉ ሌሎች አስፈላጊ የሕክምና መረጃዎችን ይዘርዝሩ።

ውሃ እና ቢቆዩ የማይበላሹ ቀላል ምግቦች

- ጥቂት የውሃ ሃይላንዶች እና ማቀዝቀዣ የማያስፈልጋቸው ምግቦችን ያካትቱ።
- የሚያበቁበት ቀናትን በመደበኛነት ይመልከቱ።

3. የሚፈልጉትን ነገሮች ይዘው መሄድ ወደሚችሉበት ቦርሳ ላይ ያዘጋጁ፦ ይዘው ይሂዱ

አሁን ያዝጋጁ

ሌሎች እቃዎች

- ተንቀሳቃሽ ሬዲዮ
- የእጅ ማብሪያዎች እና ባትሪዎች
- የመጀመሪያ ጊዜ እርዳታ ማቅረቢያ እቃዎች

በመሣሪያዎችዎ ውስጥ ምቾት ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች (ጨዋታዎች፣ መጽሐፎች፣ ምቹ ምግቦች) ማካተት ያስቡበት።

እየሄዱ ሳለ ያንሱና ይውሰዱ

- የኪስ ቦርሳ ወይም ትንሽ መያዣ እና ቁልፎች
- ስልክ እና ቻርጅ መሙያ
- መድሐኒት
- ጭንብል
- ተንቀሳቃሽ ኮምፒውተር

በቤተሰብዎ ውስጥ ላሉ ሰዎች ሌላ ምን መውሰድ እንዳለብዎት ይጻፉ። ልብሶች? የጥርስ ቡሩሾች? እርስዎ እና በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች በየቀኑ ስለሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች ያስቡ። ሕፃናት፣ የቤት እንስሳት፣ አዛውንቶች፣ እና የጤና እክል ያለባቸው ወይም አካል ጉዳተኞች ሊዘጋጁላቸው የሚገቡ ልዩ ፍላጎቶች ሊኖሯቸው ይችላል።



4. መውጣት ለማይችሉበት ድንገተኛ አደጋ ጊዜ፣ የአደጋ ጊዜ አቅርቦት ኪት ይገንቡ፦ አስፈላጊ እቃዎች

በአንዳንድ አደጋዎች፣ ቤት ውስጥ መቆየቱ የበለጠ ደኅንነቱ የተጠበቀ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ምግብዎን ለማቀዝቀዝ፣ መብራት ለማብራት ወይም ስልክዎን ለመሙላት ኤሌክትሪክ ላይኖርዎት ይችላል።

ከቤት መውጣት ለማይችሉበት ጊዜ እቃዎችን ወደ አደጋ ጊዜ አቅርቦት ኪት ያክሉ። በተቻለ መጠን ለመዘጋጀት ይሞክሩ እና ለ 2 ሳምንታት በቂ አቅራቦቶች በእጅዎ ይኑርዎት። በቤተሰብዎ ውስጥ ላሉት ሁሉ እስኪበቃ ድረስ በጥቂቱ ይቆጥቡ። የቤት እንስሳትን ማካተትዎን ያስታውሱ!

አሁን ያዝጋጁ

ዉሃ

ለአንድ ሰው በቀን 1 ጋሎን ውሃ እንዲኖርዎት ያድርጉ። የቤት እንስሳትን አይርሱ፣ እና አንዳንድ ሰዎች ተጨማሪ ውሃ ሊፈልጉ እንደሚችሉ ይወቁ (እንደ እርጉዝ ሰዎች ወይም አንዳንድ የጤና እክል ያለባቸው ሰዎች)።

በቤትዎ ውስጥ ሌሎች የውሃ ምንጮችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይወቁ እና ውሃን ለማጽዳት ጥቂት መንገዶችን ይወቁ።

ምግብ

ለማጓጓዝ ቀላል የሆነ፣ ከፍተኛ ሃይል እና ፕሮቲን ያለው እና ምንም ዓይነት ምግብ ማብሰል የማይፈልግ ምግብ ያስቀምጡ።

እርስዎ እና ቤተሰብዎ ምን በተሻለ ሁኔታ መብላት እንደሚፈልጉ ያውቃሉ።

ለቤት እንስሳት ወይም ለአገልግሎት እንስሳት ምግብ መመደብዎን ያስታውሱ።

የቆሻሻ መጣያ ከረጢቶች

ቆሻሻን ለመያዝ፣ ሰዎችን እና ነገሮችን ለማድረቅ እና ሌሎች የአደጋ ጊዜ አገልግሎቶችን ለመጠበቅ የሚያገለግሉ ተጨማሪ የፕላስቲክ ከረጢቶችን ያስቀምጡ።

በበጀትዎ ውስጥ ይቆዩ ለድንገተኛ አደጋ ኪትዎ ዝቅተኛ እና ምንም ወጪ የማይጠይቁ እቃዎች በተቀማጭ መደብሮች፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በምግብ ባንኮች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።

4. የአደጋ ጊዜ የአቅርቦት ኪት ለሚከተሉት ሁኔታዎች ያዘጋጁ መውጣት ለማይችሉባቸው ጊዜያት፦ አስፈላጊ እቃዎች

እንደ የሽንት ቤት ወረቀት ያሉ በየቀኑ የሚጠቀሙባቸውን አስፈላጊ ነገሮች ይፃፉ፣ ቤት ውስጥ ለብዙ ቀናት ከቆዩ ሊያልቁ ይችላሉ። ወደ ሱቅ መሄድ ካልቻላችሁ በአደጋ ጊዜ አቅርቦት ኪትዎ ውስጥ ትንሽ ተጨማሪ ያስቀምጡ።



5. ጓደኞች እና ጎረቤቶች እንዲዘጋጁ ይርዷቸው

ከታች ያሉትን ጥያቄዎች በሚመልሱበት ጊዜ በአደጋ ጊዜ በማህበረሰብዎ ውስጥ ማን ሊረዳዎት እንደሚችል ያስቡ።

የጎረቤቶች ስሞች እና የዕውቂያ መረጃ።

የጎረቤት ስም

የሞባይል ስልክ

የጎረቤት ስም

የሞባይል ስልክ

የጎረቤት ስም

የሞባይል ስልክ

የጎረቤት ስም

የሞባይል ስልክ

የጎረቤት ስም

የሞባይል ስልክ

የጎረቤት ስም

የሞባይል ስልክ

በቀን ጊዜያት በቤትዎ ውስጥ ማን ሊኖር ይችላል?

በቀን ጊዜያት በሰፈርዎ ውስጥ የሚኖር እርስዎን ሊረዳዎት የሚችል ሰው ማን ይገኛል?

በምሽት ጊዜያትስ? ቅዳሜ እና እሁድ ጊዜዎች ላይስ?

በእርስዎ ሰፈር ውስጥ ማን እርዳታ ሊፈልግ ይችላል?

- ✔ ከድንገተኛ ጊዜያት ወይም አደጋ ከመፈጠሩ በፊት ጎረቤቶችዎን ይወቁ። አደጋ ከመፈጠሩ በፊት እና በሚፈጠርበት ጊዜ እርስ በርስ እንዴት መረዳዳት እንዳለብዎት ይነጋገሩ።

- ✔ የጎረቤት ዝግጁነት ቡድን ለመቀላቀል ወይም ለማቋቋም ያስቡበት። የበለጠ ለማወቅ **mil.wa.gov/neighborhoods** ን ይጎብኙ።

6. በተጨማሪ ግብዓቶች የበለጠ ይማሩ፦ የደረጃ በደረጃ ዝግጁነት የቀን መቁጠሪያ



የእዚህን የቀን መቁጠሪያ እያንዳንዱን መመሪያ መከተል አያስፈልግዎትም። በራስዎ ፍጥነት በየወሩ ጥቂት እርምጃዎችን ብቻ ይውሰዱ። እርስዎ እና የሚወዷቸው ሰዎች አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ዝግጁ እንደሆናቹ በማወቅ እረፍት ማግኘት ይችላሉ።

1ኛ ወር

በቤተሰብዎ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ሰው የአደጋ ጊዜ ቦርሳ ያዘጋጁ። (ገጽ 6-7)

አካባቢያዊ የአደጋ ጊዜ ማንቂያዎች ለማግኘት በ**kingcounty.gov/alerts**ይመዝገቡ። (ገጽ 2)

2ተኛ ወር

ለቤተሰብ፣ ለጎረቤቶች፣ ለእንክብካቤ ሰጪዎች **የአደጋ ጊዜ እቅድዎን** ይፍጠሩ። (ገጽ 3፣ 5)

በእርስዎ ዝርዝር ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ስለ እቅዶችዎ ይናገሩ።

3ተኛ ወር

የተለያዩ የመልቀቂያ መንገዶችን ይወቁ እና በካርታው ላይ ምልክት ያድርጉባቸው።

የመልቀቂያ እቅድዎን ይለማመዱ። (ገጽ 4)

4ተኛ ወር

በቤት ውስጥ ደኅንነትዎ የተጠበቀ እና ምቹ ለመሆን **የአደጋ ጊዜ አቅርቦት ኪት** ማዘጋጀት ይጀምሩ። (ገጽ 8-9)

ዝግጁነት እስኪሰማዎት ድረስ በየጊዜያቱ ትንሽ ነገሮችን ያድርጉ።

5ተኛ ወር

ቤትዎን ያዘጋጁ (ገጽ 18-19)
አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን ይፈልጉ፣ የታወቁ የአደጋዎች ዝርዝሮችን ይያዙ። እነሱን ለማስተካከል እርምጃዎችን ሲወስዱ ከዝርዝርዎ ውስጥ ያሉትን አደጋዎች እንደተፈቱ ለማሳወቅ ምልክት ያድርባቸው።

6ተኛ ወር



ይድገሙት
አንዴ የዝግጁነት ደረጃዎችን ከጨረሱ በኋላ በድጋሚ ይጀምሩ! ጊዜ ያለፈባቸውን እቃዎች በዓመት አንድ ጊዜ ይፈትሹ እና ይተኳቸው። እንዲሁም ስለ ሌሎች የተሳትፎ መንገዶች ከአካባቢዎ የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ቢሮ ጋር መወያየት ይችላሉ።

6. የበለጠ ይወቁ፦ ለማንኛውም አደጋ መሠረታዊ ምክሮች

መታወቂያዎችን ይያዙ፦ አደጋ ሲከሰት ቤተሰቦች ሊለያዩ ይችላሉ። ሰዎች እና የቤት እንስሳት ሊለያዩ ይችላሉ።

- በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው መታወቂያ መያዝ አለበት።
- በልጆች የትምህርት ቤት ቦርሳዎች ውስጥ የጽሑፍ መታወቂያን ያስቀምጡ።
- የሕክምና መለያ መረጃ ወይም የእጅ ብራስሌት ማስቀመጥን/ማድረግን ያስቡበት።
- ለቤት እንስሳት የተዘመኑ መለያዎችን እና ማይክሮ ቺፖችን ያድርጉላቸው።
- የቤተሰብ እና የቤት እንስሳት ፎቶዎች በድጋሚ እንዲገናኙ ሊረዱዎት ይችላሉ።

የድጋፍ አውታር ይገንቡ፦ በአደጋ ጊዜ የመጠባበቂያ ዕቅድ ይኑርዎት። በማን ላይ መተማመን እንደሚችሉ ያስቡ።

- ከጎረቤቶችዎ ጋር ስለእራስዎ እና ስለራሳቸው ፍላጎት ይነጋገሩ።
- ከአካባቢው ውጪ ያለ ዕውቂያ ይኑርዎት።
- ወላጆችን እና ልጆችን በድጋሚ የማገናኘት ዕቅዶችን በተመለከተ ትምህርት ቤቶችን ይጠይቁ።
- በመልቀቂያ ጊዜዎች ላይ እንዲረዷቸው ችሎታ ያሏቸው ረዳቶችን እንዲኖሩ አስቀድመው ያቅዱ።
- የቤት እንስሳትዎን ለማዳን ቁልፎችን ለሚታመኑ ጓደኞች ያጋሩ።

ሌሎች ሊጠቅሙ የሚችሉ ምክሮች ዝርዝር።

-
-
-
-
-

ተጨማሪ መድሐኒቶች እና የኃይል አቅርቦት ይኑርዎት፦
ብዙ ሰዎች ያለ መድሐኒት ለሦስት ቀናት መቆየት አይችሉም። አንዳንዶች መሣሪያዎችን እና እቃዎች ለመሥራት ኤሌክትሪክ ያስፈልጋቸዋል።

- ከቤት ሲወጡ ተጨማሪ መድሐኒቶችን ይውሰዱ።
- ዶክተሮችን እና የመድሐኒት ማዘዣዎችን ጨምሮ አስፈላጊ የሕክምና መረጃ ቅጂ ይያዙ።
- ከሐኪምዎ ጋር ይነጋጋእሩ ወይም አሁንም ጥቂት ዶዝዎች ሲቀሩዎት ፋርማሲዎን በድጋሚ እንዲሞሉሎት ይጠይቁ።
- መድሐኒቱን እንደ መመሪያው ያከማቹ እና እቃዎችን እና መሣሪያዎችን ቻርጅ ያድርጉ።
- አስፈላጊ/ወሳኝ መሣሪያዎችዎን ለመሙላት እና ለማብራት የምትክ ዕቅድ ይኑርዎት።

ጭንቀትን ይቀንሱ፦ አስቀድሞ በማቀድ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጭንቀትን ይቀንሱ።

- ለተወሰኑ ልዩ ፍላጎቶች መጠለያ ለማግኘት ወደ **211** ይደውሉ።
- የአደጋ ጊዜ ቦርሳዎን በስምዎ እና በዕውቂያ መረጃዎ ይለዩ።
- ስለ ኃይል መዘጋቶች ከፍጆታ ኩባንያዎ ለሚመጡ ማንቂያዎች ይመዝገቡ።
- ልዩ የሕክምና እና የመገናኛ አቅርቦቶችን ያዘጋጁ።
- አካል ጉዳተኞችን እና የመዳረሻ እና የተግባር ፍላጎቶችን እንዴት መደገፍ እንደሚችሉ ይወቁ። ለበለጠ መረጃ **Ready.gov/Disability** ን ይጎብኙ።
- በመሣሪያዎችዎ/ኪቶችዎ ውስጥ ምቾት ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች (ጨዋታዎች፣ መጽሐፎች፣ ምቹ ምግቦች) ያካትቱ።



6. የበለጠ ይወቁ፦ ለተለያዩ ሁኔታዎች የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች

አደጋዎች ለሁሉም ሰው ፈታኝ ናቸው። እያንዳንዳችን ለአደጋ ስንዘጋጅ የተለያዩ ፍላጎቶች አለን። እርስዎ እና እርስዎ የሚያስቡላቸው ሰዎች አስቀድመው በማቀድዎ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ይዘጋጁ

ነፍሰጡር ሰዎች

በአደጋ ጊዜ እንዴት እንክብካቤ ማግኘት ወይም መውለድ እንደሚችሉ ዶክተርዎን ይጠይቁ።

መጥፎ አየርን፣ መርዛማ ውሃን፣ እና ጤናማ ያልሆነ ምግብን ለማስወገድ አስቀድመው ያቅዱ።

እርጉዝ መሆንዎን በመጠለያው ውስጥ ለሚገኙ ሠራተኞች ይንገሩ።

የጨቅላ ሕፃናት ወላጆች

የሕፃናት ምግብ ፎርሙላ የሚጠቀሙ ከሆነ በርከት ያለ ንጹህ ውሃ እና ፎርሙላ ቆጥበው ያስቀምጡ። ምንም እንኳን በመደበኛነት ባይጠቀሙበትም እንኳን ፎርሙላን እንደ ምትክ ያስቡበት።

ከሕፃኑ ጋር ረጅም ርቀት መሄድ ካለብዎት የሕፃን መያዣ ያግኙ ወይም ያዘጋጁ።

የልጅዎን ተንከባካቢ የደኅንነት እቅድ ይወቁ።

ተንከባካቢዎች

ከእንክብካቤ ተቀባይዎ ጋር የአደጋ ጊዜ ዕቅድ ይፍጠሩ።

ከራስዎ ውጪም የድጋፍ መረብ ይገንቡ።

የእንክብካቤ ተቀባይዎ የሚያስፈልጓቸውን እቃዎች እንዲያዘጋጁ እርዳታ ያቅርቡ።

ከሚያምኗቸው ሰዎች ጋር ይነጋገሩ - በጤና ክሊኒኮች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የእምነት ማህበረሰቦች፣ የጤና ድጋፍ ቡድኖች፣ እርዳታ ሰጪ የመኖሪያ ተቋማት፣ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲዎች እና ገለልተኛ የኑሮ ማዕከላት። ሊረዱ የሚችሉ አንዳንድ የደኅንነት ምክሮች እዚህ አሉ።

ይዘጋጁ

የቤት እንስሳት ወይም የአገልግሎት እንስሳት ያላቸው ሰዎች

የሚቻል ከሆነ፣ ለቤት እንስሳትዎ መለያዎችን እና ማይክሮ ቺፖችን ያድርጉላቸው።

ምግብ፣ ውሃ፣ መድሐኒት እና የክትባት ማረጋገጫዎችን ያዘጋጁ።

በአካባቢዎ ያሉትን ለቤት እንስሳት ተስማሚ የሆኑ ሆቴሎችን ይወቁ። BringFido.com፣ DogFriendly.com እና PetsWelcome.com የበለጠ ለማወቅ ሁሉም ጥሩ ግብዓቶች ናቸው። በAmericans with Disabilities Act (አሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ሕግ) መሠረት አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳት በሆቴሎች እና በመጠለያዎች ውስጥ እንዲገቡ ይፈቀዳሉ።

ትላልቅ አዋቂዎች

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ሊረዱዎት የሚችሉ የቤተሰብ፣ ጓደኞች እና ሌሎች የግል ድጋፍ አውታረ መረብ ይፍጠሩ። በሚከተለው ላይ የበለጠ ይወቁ
Ready.gov/Older-Adults.

ከስልኮችዎ አጠገብ የቤተሰብ እና የአደጋ ጊዜ ቁጥሮችን ይለጥፉ።

በጡረታዎ ወይም በአረጋውያን ማህበረሰብዎ ውስጥ ስለ ድንገተኛ አደጋ ዕቅዶች ይወቁ።

የገጠር ማህበራት

ማንቂያዎችን በስልክ መረጃ መበተኛዎች እና በሃም (በግለሰቦች የሚተዳደር) ሬዲዮ አውታረ መረቦች ያጋሩ።

እንዴት እርስ በርስ መደጋገፍ እንደሚችሉ ለመወያየት ከጎረቤቶችዎ ጋር ይገናኙ።

6. የበለጠ ይወቁ፦ ለተለያዩ ሁኔታዎች የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች

ለተጨማሪ ግብዓቶች እና ስለ ዝግጁነት ጠቃሚ ምክሮች፣ እባክዎ በአካባቢዎ የሚገኘውን ገለልተኛ የመኖሪያ ማዕከል ያግኙ። **በWASILC.org ላይ የበለጠ ይወቁ**

ቀድመው ያቅዱ



የእድገት እክል ያለባቸው ሰዎች
በአደጋ ጊዜ ሊተማመኑባቸው የሚችሏቸው የታመኑ አጋሮችን ይለዩ።

ከእርስዎ የድጋፍ አውታር ጋር አብረው ዕቅድ ያውጡ።

ደኅንነት እንዲሰማዎት ለማገዝ ዕቅድዎን ይለማመዱ።

የንግግር እና የመግባቢያ እክል ያለባቸው ሰዎች
ሌሎች ከእርስዎ ጋር እንዴት መገናኘት/መነጋገር እንደሚችሉ የሚገልጽ የመመሪያ ካርድ ይያዙ።

የመገናኛ መሣሪያዎችን፣ የሐረግ ካርዶችን ወይም የሥዕል ሰሌዳዎችን ይያዙ።

የረዳት መሣሪያዎ ከተበላሸ ወይም ከጠፋ እንዴት እንደሚተኩት ይወቁ።

የእንቅስቃሴ እና ሌሎች አካላዊ እክል ያለባቸው ሰዎች
ለትራንስፖርት አገልግሎቶች ከታመኑ አጋሮች ጋር አስቀድመው ያቅዱ።

ለተበላሹ ራምፖች ወይም የባቡር ሐዲዶች እቅድ ያውጡ።

ደኅንነትዎ እንደተጠበቀ ለመውጣት ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት በተቻለ ፍጥነት ከቤትዎ ይውጡ።

ስለ ልዩ የአካል ጉዳቶች እና ለአካል ጉዳተኞች ዝግጁነት መረጃ የበለጠ መመሪያ ለማግኘት **Ready.gov/Disability** ን ይጎብኙ።

ቀድመው ያቅዱ

ውስን መጓጓዣ ላሏቸው ሰዎች
መልቀቅ ካለብዎት የመኪና መጋርት አገልግሎትን ያዘጋጁ።

የሕዝብ ትራንስፖርት ለመጠቀም ያስቡ - ከተፈጥሮ አደጋ በኋላ ነጻ ሊሆን ይችላል።

ተደራሽ ለሆነ ትራንስፖርት አስቀድመው ያቅዱ።

Limited English Proficiency (የተገደበ የእንግሊዝኛ ችሎታ) ያላቸው ሰዎች
ስለ ደኅንነት አማራጮች ለመነጋገር የታመኑ የማህበረሰብ ምንጮችን ያግኙ።

የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች የአደጋ ጊዜ መረጃን ለእርስዎ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው።

የትኞቹ ምንጮች የአደጋ ጊዜ ማንቂያዎችን እና መረጃዎችን እንደሚሰጡ ለማወቅ የሚከተሏቸውን ዜና እና ማህበራዊ ሚዲያዎች ይመርምሩ።

ለአካባቢው አዲስ ለሆኑ ሰዎች
እንደ ለአደጋ ጊዜ ማንቂያዎች መመዝገብ ያሉ የአደጋ ጊዜ ሥርዓት መሠረታዊ ነገሮችን ይወቁ።

ስለአካባቢው አደጋዎች ይወቁ።

ለትክክለኛ የአደጋ ጊዜ መረጃ ታማኝ ምንጮችን ያግኙ።

6. የበለጠ ይወቁ፦ ቤት ውስጥ አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮችን መለየት

በደንገተኛ አደጋዎች እና በአደጋ ጊዜ ቤትዎ ደኅንነቱ የተጠበቀ ቦታ መሆኑን ያረጋግጡ። ቤት ውስጥ አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮችን ለይተው በማስተካከል ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ያስወግዱ እና ያስተካክሉ።

✅ **በአካባቢዎ ስላሉት አደጋ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነገሮች ያስቡ - በቤትዎ ውስጥ አንዳንድ አደጋዎችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች አሉ?**

- **ወደ እያንዳንዱ ክፍል ገብተው ያስቡ፦**
  - አሁን የመሬት መንቀጥቀጥ ቢፈጠርስ?
  - ኃይል/መብራት ቢጠፋስ?
  - በዚህ ክፍል ውስጥ እሳት ቢነሳስ?
- **ይበልጥ ደኅንነታቸው የተጠበቀ መደረግ ያለባቸውን እቃዎች ዝርዝር ያዘጋጁ።**

ለመጀመር እንዲችሉ የሐሳቦች ዝርዝር እዚህ ይገኛሉ

በእያንዳንዱ የቤቱ ክፍል ውስጥ፦

✅ **አጠቃላይ ደኅንነት፦**

- በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ ሊወድቁ የሚችሉ ወይም በሕፃናት ሊጎተቱ ወይም ሊወድቁ የሚችሉ እንደ የመጽሃፍ መደርደሪያ፣ ቁምሳጥኖች እና የውሃ ማሞቂያ ያሉ የቤት እቃዎችን እና ትላልቅ እቃዎችን ጥንቃቄ ባለው መልኩ ያቆዩ።
- እንደ የጥበብ ሥራዎች እና ፎቶግራፎች፣ ቴሌቪዥን፣ በመደርደሪያዎች ላይ ያሉ ትልልቅ ዕቃዎችን እና በግድግዳዎች ላይ የተንጠለጠሉ ወይም የተጣበቁ ነገሮችን ጥንቃቄ ባለው መልኩ ያቆዩ።
- ሲራመዱ ሊጥልዎት የሚችሉ እቃዎችን ለመከላከል የቦታ ምንጣፎችን እና የወለል ንጣፎችን ጥንቃቄ ባለው መልኩ ያንጥፉ።

✅ **የእሳት አደጋ ደኅንነት፦**

- የሚሠሩ የጭስ እና የካርቦን ሞኖክሳይድ መመርመሪያዎች እንዳሉዎት ያረጋግጡ። አስፈላጊ ከሆነ ድጋፍ ለማግኘት የአካባቢዎን የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል ያነጋግሩ።
- የሚሠራ የእሳት ማጥፊያ እንዳለዎት ያረጋግጡ እና እንዴት እንደሚጠቀሙበት ይወቁ።

✅ **የኤሌክትሪክ ደኅንነት**

- የኤሌክትሪክ ፓነልዎ በቀላሉ ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጡ።
- የኤሌክትሪክ ገመዶችን እና ሶኬት መሰኪያዎችን ይፈትሹ።
  - ሶኬት መሰኪያዎች ላይ ከመጠን በላይ የሆነን ጭነት ያስወግዱ፣ ተጨማሪ የሶኬት መሰኪያዎች ቦታ አስፈላጊ ከሆነ የኃይል ማከፋፈያን ይጠቀሙ።
  - ብዙ የኤክስቴንሽን ገመዶችን አንድ ላይ ከማገናኘት ይቆጠቡ። እንዲሁም የኃይል ማከፋፈያዎችን ከሌሎች የኃይል ማከፋፈያዎች ጋር አያገናኙ።
  - የሚንጠለጠሉ ገመዶችን ያስወግዱ። በገመድ ክሊፖች፣ በኮንዲቶች ወይም በፕላስተሮች በግድግዳዎች እና ወለሎች ላይ ገመዶችን በአግባቡ ያስቀምጡ። ተጨማሪ ገመዶችን ንፁህ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ይጠምጥሙ።

✅ **የቤት ማሻሻያዎች ላይ ኢንቨስት ያድርጉ፦** ለGCFI (Ground Fault Circuit Interrupters (ወደ ምድር ውስጥ ከልክ በላይ የሚኖሩ ኤሌክትሪክ ማስወገጃ መንገዶችን የሚያቋርጡ ነገሮች)) የኤሌክትሪክ ማሰራጫዎችን በኩሽና፣ በመታጠቢያ ቤቶች እና በሌሎች የውሃ ምንጮች አጠገብ ይመልከቱ/ይፈትሹ።

በቤትዎ እያንዳንዱን ክፍል ውድጥ የሚከተሉትን ለማድረግ ግምት ውስጥ ያስገቡ፦

በኩሽና ውስጥ፦

- በኩሽናዎ ውስጥ ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የተከማቸ እና በቀላሉ ሊደረስበት የሚቻል የABC እሳት ማጥፊያ እንዳለዎት ያረጋግጡ።
  - የምግብ ማብሰያ ቦታዎች ላይ ለሚከሰት እሳት ለማጥፋት ሌሎች ሁለት መንገዶችን ይማሩ፦ ምግብ በሚዘጋጅበት ጊዜ የድስቱን ክዳን ይዘጉ፣ ቤኪንግ ሶዳ ወይም ዱቄት በአቅራቢያ ያስቀምጡ።
- የቤት ኬሚካሎች እና ማጽጃዎች ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ተከማችተው ልጆች እና የቤት እንስሳት በማይደርሱባቸው ቦታ ያቆዩ። በማጠራቀሚያው አካባቢ መጨናነቅን ያስወግዱ፣ ምርቶች ትክክለኛ መለያዎችን እንዳላቸው ያረጋግጡ እና ኬሚካሎችን ወይም ማጽጃዎችን በጭራሽ አይቀላቀሉ።
- ስለታም ቢላዎች እና እቃዎች ድኅንነታቸው በተጠበቀበት ቦታ ላይ መቀመጣቸው ያረጋግጡ።

ሳሎን ወይም የቤተሰብ ክፍል ውስጥ፦

- የእሳት አደጋዎችን እንዲኖሩ የሚያስችሉ ነገሮችን ይወቁ። ለሙቀት የሚሆን እሳት የሚቀጣጠልበት ቦታ አለ? በቤተሰቡ ውስጥ ሻማ የሚያበራ ሰው አለ? ሲጋራ የሚያጨስ ሰው አለ? መብራቶች እና ማሞቂያዎች ከመጋረጃዎች እና ሌሎች ለስላሳ ጨርቆች አስተማማኝ ርቀት ላይ ናቸው?

በመኝታ ክፍሎች ውስጥ፦

- መውጫ መንገዶች ላይ መሰናክል እንደሌላ ያረጋግጡ። ሊወድቁ እና መውጫዎን ሊገድቡ የሚችሉ ትልልቅ የቤት እቃዎችን ወይም ነገሮችን ያስተካክሉ።
- የሙቀት ምንጮች በሰዓት ቆጣሪዎች ቁጥጥር ሥር መሆን አለባቸው እና ሊነዱ ከሚችሉ ነገሮች መራቅ አለባቸው።

በልብስ ማጠቢያ ወይም የመገገያ ክፍሎች ውስጥ፦

- የሊንት ገዳቢዎችን ግልጽ እና ተግባራዊ እንደሆኑ ያቆዩ። የአየር ማናፈሻ ቱቦው እንዲሁ በንጽህና መያዙን ያረጋግጡ።
- ትላልቅ መገልገያዎችን በማሰሪያዎች ይሰሩ።
- ማጽጃዎችን እና ኬሚካሎችን በጥንቃቄ ያስቀምጡ።

በጋራዥ፣ መጠለያ፣ እቃ ማስቀመጫ ክፍል ወይም ማከማቻ ቦታ ውስጥ፦

- እንደ ዘይቶች እና ቤንዚን ያሉ ኬሚካሎች እና አደገኛ ቁሶች ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መቀመጥ፣ በደንብ መታሸግ እና ግልጽ በሆነ መልኩ መሰየም አለባቸው። አካባቢውን ከቆሻሻ ማጽዳት እና ሁሉንም እቃዎች ሕፃናት በማይደርሱበት ቦታ ያስቀምጡ።
  - ያገለገሉ ዘይት ወይም ቅባት ያላቸው ጨርቆች በታሸገ የብረት መያዣ ውስጥ ያከማቹ።
  - ጥቅም ላይ ያልዋሉ ኬሚካሎችን እና ነዳጆችን በትክክል ያስወግዱ።
- መደርደሪያዎች እና ሌሎች የቤት እቃዎች ደኅንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀመጣቸውን ያረጋግጡ።
- የእግረኛ መንገዶችን ሁኔታ ይጠብቁ እና አስፈላጊ ከሆነ መሣሪያዎች ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጡ።
- የኃይል መሣሪያዎችን ሲጠቀሙ እና ሲያከማቹ የአምራቾችን የደኅንነት መመሪያዎችን ይከተሉ።

የቤትዎን ዕድሜ ግምት ውስጥ ያስገቡ። ለቤቶች መዋቅራዊ የመሬት መንቀጥቀጥ ደኅንነት በድጋሚ ማስተካከል ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል።
የበለጠ ለማወቅ ወደ **www.wabo.org/earthquake-home-retrofit** ይሂዱ።

በቤትዎ ውስጥ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ሌሎች ነገሮች

7. አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ፦ የደኅንነት ምክሮች፦ የመሬት መንቀጥቀጥ

ከመከሰቱ በፊት



ረዣዥም እና ከመጠን በላይ ትልቅ የሆኑ የቤት እቃዎችን በግድግዳዎች ላይ በደንብ ያጣብቁ።

በግድግዳዎች ላይ የተንጠለጠሉ እቃዎችን ደኅንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ ያቆዩ። ከባድ እና ሊሰበሩ የሚችሉ እቃዎችን ደኅንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ ያቆዩ ወይም ከመሬት ወለል ቅርብ ወደሆኑ መደርደሪያዎች ይውሰዱ።

ለመሬት መንቀጥቀጥ ማንቂያዎች ነፃውን MyShake መተግበሪያ ያግኙ።

ወደመሬት መጠጋት፣ መሸፈን እና መቆየት ይለማመዱ።

ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ እና ውሃ እንዴት ማጥፋት እንደሚችሉ ይወቁ።

እየተከሰተ ሳለ

ወደ ውጪ ለመውጣት አይቸኩሉ። ከጠረጴዛ ወይም ከዴስክ ሥር ይሁኑ።

አልጋ ላይ ከሆኑ በሆድዎ ይሁኑ እና ጭንቅላትዎን እና አንገትዎን በትራሱ ይሸፍኑ።



ውጭ ከሆኑ ሊወድቅ ከሚችል ማንኛውም ነገር ይራቁ።

እየነዱ ከሆነ መኪናውን በጥንቃቄ ያቁሙት እና ከሕንፃዎች፣ ዛፎች፣ ድልድዮች፣ የኤሌክትሪክ መስመሮች እና ሌሎች መዋቅሮች ይራቁ።

ቤት ውስጥ ከሆኑ እዛው ይሁኑ። በሮች አካባቢ አይቅረቡ።

የደኅንነት ምክሮች፦ የመሬት መንቀጥቀጥ

ከተከሰተ በኋላ

ለድጋሚ ዳግም መንቀጥቀጦች ዝግጁ ይሁኑ እና ሊከሰት ለሚችለው ሱናሚ ይዘጋጁ።

ጉዳት እንደደረሰብዎ ለማወቅ እራስዎን ይፈትሹ።

አደጋዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮችን ይፈትሹ።

የተጎዳ ሕንፃ ውስጥ ከሆኑ ወደ ውጭ ይውጡ።

መውጣት ካልቻሉ፣ ያሉበትን አካባቢ ለማመልከት አጭር የጽሑፍ መልዕክት ይላኩ ወይም ድምጽ ያሰሙ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

ጠቃሚ ምክር፦ ስለ የመሬት መንቀጥቀጥ መድን ከመድን ወኪልዎ ጋር ይነጋገሩ።

የደኅንነት ምክሮች፦ የኃይል መቋረጥ

ከመከሰቱ በፊት



የእጅ ባትሪዎችን እና ፋኖሶችን ያዘጋጁ - ሻማ አይመከርም።

ተንቀሳቃሽ ባትሪ መሙያዎችን ሞልተው ዝግጁ ያድርጉ።

የመኪና ጋዝ ታንክዎን ቢያንስ በግማሽ ይሙሉ።



የማይበላሽ እና መብሰል የማይፈልግ ምግብን ይግዙ።

መብራት/ኃይል መቆራረጥ ሲኖር ምግብ እና መድሐኒቶችን እንዴት ቀዝቃዛ ማድረግ እንደሚችሉ ይወቁ።

እየተከሰተ ሳለ



ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል ዕቃዎችን እና ኤሌክትሮኒክስን ይንቀሉ።

አንድ መብራት እንደበራ ያቆዩ።

ምግብን እንደቀዘቀዘ ለማቆየት ፍሪጅዎን እና ማቀዝቀዣዎን ከመክፈት ይገደቡ።

ጄነሬተሮችን፣ የካምፕ ምድጃዎችን፣ እና ግሪሎችን ከቤት ውጭ እና ከመስኮቶች እና የአየር ማናፈሻ ሥርዓቶች ደኅንነታቸው በተጠበቀ ርቀት ላይ ይጠቀሙ።



የጋዝ ምድጃዎን ለሙቀት ዓላማዎች አይጠቀሙ።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ

አጠራጣሪ ወይም የተበላሹ ምግቦችን ያስወግዱ።

ዕቃዎችን እና ኤሌክትሮኒክስን ይሰኩ እና ያብሩ።

ያገለገሉ ዕቃዎችን በድጋሚ ቀይረው ያከማቹ።

ተንቀሳቃሽ የባትሪ መሙያዎችን በድጋሚ ይሙሉ።

በአካባቢዎ ያሉ የኤሌክትሪክ አደጋዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮችን ይወቁ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

አስፈላጊ ለሆኑ የሕክምና መሣሪያዎች በኃይል እና በኤሌትሪክ ላይ የሚተማመኑ ከሆነ አስቀድመው ያቅዱ። ተጨማሪ ባትሪ ይኑርዎት ወይም አማራጭ የመሙያ ዘዴዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙ ይወቁ።

የደኅንነት ምክሮች፦ የሳይበር ጥቃቶች

ከመከሰቱ በፊት

ጠንካራ የይለፍ ቃሎችን ይጠቀሙ፣ ተደጋጋሚ የይለፍ ቃላትን ያስወግዱ፣ ባለብዙ ደረጃ ማረጋገጫን ይጠቀሙ።

የባንክ እና የብድር እንቅስቃሴን በመደበኛነት ይፈትሹ።

በመስመር ላይ የሚያጋሯቸውን የግል መረጃዎች ይገድቡ።

የቤት አውታርዎን ደኅንነት ይጠብቁ። ለፋይሎችዎ በመደበኛነት ምትኬ ያስቀምጡላቸው።

አጠራጣሪ አገናኞችን በጭራሽ አይጫኑ ወይም ከማያውቋቸው ሰዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ አይስጡ።

እየተከሰተ ሳለ

በእርስዎ መለያዎች (ባንኮች፣ ክሬዲት፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ኢሜይል፣ ወዘተ) ላይ አጠራጣሪ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት ያድርጉ።

ለሁሉም የመስመር ላይ መለያዎች የይለፍ ቃሎችን ወዲያውኑ ይለውጡ።

መሣሪያውን ለማጥፋት ያስቡበት እና ለመቃኘት እና ለማስተካከል ወደ ባለሙያ ይሂዱ።

የሥራ፣ የትምህርት ቤት ወይም የሌላ የሥርዓት ተጠቃሚዎች እንዲያውቁ ያድርጉ።

እርዳታ ለመጠየቅ ፍርሃት አይሰማዎት፣ የሳይበር ጥቃቶች የተለመዱ ናቸው።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ

የማንነት ስርቆት ጥበቃ ፕሮግራም ውስጥ ይመዝገቡ።

የይለፍ ቃላትን በመደበኛነት ለማዘመን አስታዋሾችን ያዘጋጁ።

ተሞክሮዎን ለጓደኞች እና ለቤተሰብ ያካፍሉ።

ጉዳት ደርሶባቸው ሊሆኑ ለሚችሉ ዕውቂያዎችን ያሳውቁ።

በመሣሪያዎች እና በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የግላዊነት ቅንብሮችን ይገምግሙ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የደኅንነት ምክሮች፦ ወረርሽኝ

ከመከሰቱ በፊት

የጤና መድን ፖሊሲዎችን ይገምግሙ እና ይረዱ።

በሽታዎች እንዴት እንደሚተላለፉ ይወቁ።

የበሽታ መከላከያ መንገዶችን ይወቁ እና በተግባር ይለማመዱ።

ወቅታዊ ክትባቶችን እና ማበረታቻዎችን ይውሰዱ።

በይለፍ ቃል የተጠበቁ የሕክምና እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን ዲጂታል ቅጂዎችን ይፍጠሩ።

እየተከሰተ ሳለ

ከታመሙ ወይም ምልክቶች እየተመለከቱ ከሆነ ቤት ውስጥ ይቆዩ።

ደኅንነትን እና ጤናን እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ የቅርብ ጊዜ የጤና ባለስልጣናት መመሪያዎችን ይከተሉ።

ጥሩ የግል ጤና ልማዶችን ይጠብቁ።

ስለ በሽታው ትክክለኛ መረጃ ያካፍሉ።

መጨነቅ እና መወጠር የተለመደ ነው።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ

የመከላከያ እርምጃዎችን መውሰድዎን ይቀጥሉ።

ስለተማሯቸው ትምህርቶች ከቤተሰብዎ ጋር ይነጋገሩ፣ ካስፈለገ የድንገተኛ አደጋ ዕቅድዎን ያዘምኑ።

በሚመከሩት ክትባቶች እና ማበረታቻዎች ላይ የሕዝብ ጤና መመሪያዎችን መከተልዎን ይቀጥሉ።

ማህበረሰብዎ ከወረርሽኙ ተጽዕኖ እንዲያገግሙ የሚረዱበትን መንገዶች ይወቁ።

ሌሎችን ለማስተማር ተሞክሮዎን ያካፍሉ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የደኅንነት ምክሮች፦ የክረምት የአየር ሁኔታ

ከመከሰቱ በፊት

የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን ይከታተሉ።
ለክረምት አውሎ ነፋሶች የተጋላጭነት ስጋትዎን ይወቁ።

አስፈላጊ አቅርቦቶችን አስቀድመው ይግዙ።

ቤትዎን እና ተሽከርካሪዎን ለአውሎ ንፋስ እና ለበረዷማ የሙቀት መጠን ያዘጋጁ።

ለብዙ ቀናት ቤት ውስጥ ሆነው ለቆየት ይዘጋጁ።

ከጉንፋን ጋር የተዛመዱ በሽታዎች ምልክቶችን ይወቁ።

እየተከሰተ ሳለ

ቤት ይቆዩ፣ ከቻሉ ከመጓዝ ይቆጠቡ።

ከቤት ውጭ የሚያሳልፉትን ጊዜ ይገድቡ፣ ደራርበው ይለብሱ።

ጄነሬተሮችን እና ግሪሎችን ከቤት ውጭ ብቻ ይጠቀሙ።

ጎረቤቶችዎን ይመልከቱ።

ከጉንፋን ጋር የተዛመዱ በሽታዎች የሚያሳዩት ምልክቶች ያሉ እንደሆነ ይመልከቱ።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ

የእግረኛ መንገዶችን እና የመራመጃ መንገዶችን ከቤትዎ ውጭ እንዳይጨናነቁ ያድርጉ።

ያገለገሉ አቅርቦቶችን ይተኩ።

ለተጨማሪ የአየር ሁኔታ ጉዳዮች ዝግጁ ይሁኑ።

በቤትዎ አጠገብ አደጋዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮች መኖራቸውን ያረጋግጡ (እንደ የወደቁ ዛፎች፣ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ ትራፊክ፣ ወዘተ)።

ቤትዎ መጎዳቱን ያረጋግጡ፣ የካርቦን ሞኖክሳይድ ጠቋሚዎች አሁንም እየሠሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

....

....

....

....

....

....

....

የደኅንነት ምክሮች፡- ጎርፍ

ከመከሰቱ በፊት

የከባድ ዝናብ ቱቦዎች እና የፍሳሽ ማስወገጃዎችን ያፅዱ።

ሰነዶችን እና አስፈላጊ ዕቃዎችን ለመጠበቅ ከውሃ የሚከላከሉ መያዣዎችን ይጠቀሙ።

የጎርፍ መድን ያግኙ። አስፈላጊ ዕቃዎችን ፎቶ ያንሱ።

የመኪና ጋዝ ታንክዎን ቢያንስ በግማሽ ይሙሉ።

ወደ ከፍተኛ ቦታ የሚወስዱ የማምለጫ መንገዶችን ይወቁ።

እየተከሰተ ሳለ

ቤት ይቆዩ፣ ከቻሉ ከመጓዝ ይቆጠቡ።

እየጎረፈ በሚሄድ ውሃ ውስጥ በጭራሽ አይራመዱ ወይም አይዋኙ። 6 ጫማ ጥልቀት ያለው የሚንቀሳቀስ ውሃ አዋቂን ሊጥል ይችላል።

እየጎረፈ በሚሄድ ውሃ ውስጥ ከመንዳት ይቆጠቡ። 12 ጫማ ጥልቀት ያለው የሚንቀሳቀስ ውሃ መኪናን ጠራርጎ ሊወስድ ይችላል።

ሊከሰቱ ለሚችሉ የጭቃ መንሸራተቶች እና የመሬት መንሸራተቶች ይጠንቀቁ።

ለአየር ሁኔታ ዝመናዎች እና ለአደጋ ጊዜ ማንቂያዎች ትኩረት ይስጡ።

በፍጥነት የሚንቀሳቀስ ውሃ እያለ ከተሽከርካሪ ውስጥ መውጣት ካቃትዎት፣ በተሽከርካሪው ውስጥ ይቆዩ። ውሃው እየጨመረ እየመጣ ከሆነ ወደ ጣሪያው ይጡጉ።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ

የሚጎርፍ ውሃ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ እንደሚችል ግምት ውስጥ ያስገቡ።

በሚጎርፍ ውሃ ውስጥ ከመሄድ ወይም ከመንዳት ይቆጠቡ። የሚጎርፉ ውሃዎች የተበከሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ባለስልጣናት ደኅንነቱ የተጠበቀ ነው እስከሚሉ ድረስ ከአደጋ ጊዜ አካባቢዎች አይመለሱ።

በቤትዎ ውስጥ ተባዮች እና ምናልባትም የተበከሉ ነገሮች እንዳይኖሩ ይጠንቀቁ።

ማንኛውንም ጉዳት ይመዝግቡ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?



የደኅንነት ምክሮች፦ ከልክ ያለፈ ሙቀት

ከመከሰቱ በፊት

የአየር ማቀዝቀዣ ካለዎት በመደበኛነት ያስተካክሉት።

ቤትዎን ቀዝቃዛ ለማድረግ ተጨማሪ መንገዶችን ይወቁ።

የሚወዷቸውን ሰዎች እና ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጎረቤቶችን በመደበኛነት ይመልከቱ።

ከሙቀት ጋር የተያያዙ ምልክቶችን እና ጠቋሚዎችን ይወቁ።

እንደ የገበያ ማዕከሎች፣ የፊልም ቲያትሮች እና ቤተመጻሕፍት ያሉ አየር ማቀዝቀዣ ያላቸው በአቅራቢያ ያሉ ቦታዎችን ይለዩ፣ እርስዎ ቀዝቃዛ ሆነው እንዲቆዩ ወደነዚህ ቦታ መሄድ ይችላሉ።

እየተከሰተ ሳለ

ተጨማሪ ውሃ እና የስኳር ወይም ካፊይን ይዘት የሌላቸው መጠጦችን ይጠጡ።

ከቤት ውጭ ወይም ከፍተኛ የኃይል እንቅስቃሴዎች ያሉባቸው ቦታዎች ጋር ከመሄድ ይቆጠቡ።

ስስ፣ ቀላል ክብደት ያለው፣ ነጣ ያለ ቀለም ያለው ልብስ ይልበሱ።

የሚወዷቸውን ሰዎች እና ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጎረቤቶችን በመደበኛነት ይመልከቱ።

ከሙቀት ጋር የተያያዙ ምልክቶችን እና ጠቋሚዎችን ይመልከቱ፣ አስፈላጊ ከሆነ የሕክምና እርዳታ ያግኙ።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ



ከተከሰተ በኋላ

ዕቃዎችን በድጋሚ ቀይረው ያከማቹ።

የሚወዷቸውን ሰዎች እና ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጎረቤቶችን በመደበኛነት መመልከትን ይቀጥሉ።

አስፈላጊ ከሆነ የሕክምና እርዳታ ይፈልጉ።

በማርገብገቢያዎች እና በአየር ማቀዝቀዣዎች ውስጥ ማጣሪያዎችን ያጽዱ እና ይቀይሩ።

ከሙቀት ጋር የተያያዙ ምልክቶችን እና ጠቋሚዎችን መከታተልዎን ይቀጥሉ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የደኅንነት ምክሮች፦ የጭስ/የአየር ጥራት

ከመከሰቱ በፊት

ለማህበረሰብዎ የማስጠንቀቂያ እና የማሳወቂያ ሥርዓት ይመዝገቡ።

የአየር ጥራት መረጃን እና ትንበያዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይወቁ።

የቤት HVAC እና የአየር ማጣሪያዎች ንፁህ መሆናቸውን እና በየጊዜው መለወጣቸውን ያረጋግጡ።

አስፈላጊ ከሆነ የDIY ማጣሪያ ማርገብገቢያ መገንባት እንዴት እንደሚቻል ይወቁ።

በቤት እና በተሽከርካሪዎች ውስጥ የN95 ጭምብሎችን ያከማቹ።

እየተከሰተ ሳለ

የአየር ጥራት መረጃን እና ትንበያዎችን ይከታተሉ።

የስሜት ሕዋሳትዎን ይመኑ - ማየት፣ መቅመስ ወይም ማሽተት ከቻሉ፣ ውስጥ መሆን አለብዎት።

አካላዊ እንቅስቃሴን ይቀንሱ።

ከቤት ውጭ ጊዜን ከማሳለፍ ይቆጠቡ፣ ውጭ መሆን ካለብዎት የመከላከያ ጭንብል ያድርጉ።

አደጋን የሚጨምሩ ነገሮችን ይወቁ - በዕድሜ እና በጤና ላይ በመመሥረት የቤተሰብዎን ስጋትዎች ይወቁ።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ



ከተከሰተ በኋላ

ያገለገሉ ዕቃዎችን በድጋሚ ቀይረው ያከማቹ።



በHVAC ወይም በማጣሪያ ማርገብገቢያዎች ውስጥ ያሉ የአየር ማጣሪያዎችን ይለውጡ።

ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ የጤና ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይወቁ።

ስለተማሯቸው ትምህርቶች ከቤተሰብዎ ጋር ይነጋገሩ፣ ካስፈለገ የድንገተኛ አደጋ ዕቅዶችን ያዘምኑ።

የተሰበሰበውን አመድ ወይም አቧራ ለማስወገድ የቤት ውስጥ ንጣፎችን ያፅዱ። በሚያፀዱ ጊዜ ማንኛውንም ቅንጣቶች ወደ ውስጥ እንዳይተነፍሱ ጭምብል ያድርጉ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የደኅንነት ምክሮች፦ የዱር እሳቶች

ከመከሰቱ በፊት



ቀይ ባንዲራ ማስጠንቀቂያ ማለት አሁን መዘጋጀት አለብዎት ማለት ነው።



ለኤሌክትሪክ/ኃይል መቆራረጦች ዕቅድ ያውጡ። ሻማዎችን አይጠቀሙ።

የመኪና ጋዝ ታንክዎን ቢያንስ በግማሽ ይሙሉ።

የአስፈላጊ ሰነዶችን ቅጂዎች ያዘጋጁ።

በቤትዎ እና በአትክልት ቦታዎ መካከል ክፍተት ይፍጠሩ።

እየተከሰተ ሳለ

“ሲደርስ እሄዳለው” አይበሉ። ሲነገርዎ ይውጡ!

ጭስ ካለ፣ ጭምብል ይጠቀሙ። ከተቻለ በቤት ውስጥ ይቆዩ።

ሁሉንም በሮች እና መስኮቶች ይዝጉ።

ለተጨማሪ መመሪያዎች የአደጋ ጊዜ ዜናዎችን እና ማንቂያዎችን ያዳምጡ።

የቤት እንስሳትን ለአደጋ ጊዜያት ያዘጋጁ።

ጠቃሚ ምክር፦ ለበለጠ የዱር እሳት ደኅንነት ምክሮች የFireWise ፕሮግራምን በ **nfpa.org/public-education ውስጥ ይመልከቱ**

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ

ያገለገሉ ዕቃዎችን በድጋሚ ቀይረው ያከማቹ።



በHVAC ወይም በማጣሪያ ማርገብገቢያዎች ውስጥ ያሉ የአየር ማጣሪያዎችን ይለውጡ።

ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ የጤና ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይወቁ

ስለተማሯቸው ትምህርቶች ከቤተሰብዎ ጋር ይነጋገሩ፣ ካስፈለገ የድንገተኛ አደጋ ዕቅዶችን ያዘምኑ።

ባለስልጣናት ደኅንነቱ የተጠበቀ ነው እስከሚሉ ድረስ ከአደጋ ጊዜ አካባቢዎች አይመለሱ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የደኅንነት ምክሮች፦ መዋቅራዊ እሳት

ከመከሰቱ በፊት

ወደ 911 እንዴት እንደሚደውሉ ይወቁ። የመድን ፖሊሲዎ ወቅታዊ መሆኑን ያረጋግጡ።



የቤተሰብ የመልቀቂያ ዕቅድ ያዘጋጁ እና ይለማመዱ። የመሰብሰቢያ ቦታ እና ከእያንዳንዱ ክፍል ቢያንስ ሁለት የመውጫ መንገዶችን ያካትቱ።

በቤትዎ ውስጥ የጭስ እና የካርቦን ሞኖክሳይድ መመርመሪያዎችን ይጫኑ። በዓመት ሁለት ጊዜ ባትሪዎችን ይፈትሹ።

የቤት ውስጥ እሳት ማጥፊያ ይኑርዎት እና እንዴት እንደሚጠቀሙበት ይወቁ።



የመኝታ ክፍል በሮችን ዘግተው ይተኙ፤ ከአልጋዎ በታች ጥንድ ጫማዎችን ያቆዩ።

እየተከሰተ ሳለ

ወደ 911 ይደውሉ።

ለቀው ይውጡ። ሲወጡ በሮችን እና መስኮቶችን ይዝጉ።

መውጣት ካልቻሉ በርዎ መዘጋቱን ያረጋግጡ። አካባቢዎን ለመጀመሪያ ደረጃ ምላሽ ሰጪዎች ያሳውቁ።

ሁሉም የቤተሰብ አባላት እና የቤት እንስሳት ከቤት ውጭ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

አንዴ ከወጡ በኋላ በድጋሚ ወደ ሕንፃው አይግቡ። ከመጀመሪያው ምላሽ ሰጪዎች ጋር ይገናኙ።

አካባቢዎ ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አደጋዎች ይዘጋጁ

ከተከሰተ በኋላ



የመድን ኩባንያዎን ያነጋግሩ እና ጉዳቶችን ይመዝግቡ።

ለእርዳታ የአካባቢ ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና ፕሮግራሞችን ይመርምሩ።

የጭስ እና የካርቦን ሞኖክሳይድ መመርመሪያዎችን ይተኩ።

ደኅና መሆንዎን ለማሳወቅ ቤተሰብ እና ጓደኞችን ያግኙ።



የተማሩትን ይከልሱ እና የመልቀቂያ ዕቅዶችን ያስተካክሉ።

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የደኅንነት ምክሮች፦

ከመከሰቱ በፊት

እየተከሰተ ሳለ

የደኅንነት ምክሮች፦

ከተከሰተ በኋላ

ይህ ተከስቶ ነበር?

ምን ሠርቷል ወይም አልሠራም? ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ ይችላሉ?

ተጨማሪ ማስታወሻዎች

www.kingcounty.gov/prepare

King County
Emergency Management